# የአማርኛ ፈሊጦች

ከ

አምሳሉ አክሊሉ እና ዳኛቸው ወርቁ

፪ኛ እትም

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፩፱፻፹፫

30/9/85

ዲሁ። ሆኖም እዚህ ላይ፥'ተመሳሳይ እሳቤ' ስንል፥ በነገሮች መካከል የሚኖረውን ተመሳሳይነት ብቻ እንዳልሆነ ማጤን ያስፈልጋል ። ተመሳሳይነቱ በነገሮችና በረቂቅ ባሕርይ ወይም ሁናቴ መካከልም ሊሆን ይችላል ፤ ለምሳሌ ፥ ቁልፍ ሐሳብ ፥ የመፍትሔ ቁልፍ ፥ ሽርሙጣ ቁልፍ እያሰኘ ። የሚሠራባቸው ቃላት ስምና ስም መሰሎችም ብቻ መሆን አይኖርባቸውም ። በግሶችም መጠቀም ይቻላል ፤ ለምሳሌ ፥ አእምሮው ደነዘ ፥ አንጀቱ አረረ ፥ በስሜት ተቃጠለ እና የመሳሰሉት ።

ፈሊጣዊ አነጋገር ፥ ባረጁ ባፈጁ ቃላት እና/ወይም ትርጉሞች ይጠቀማል ፤ ማለትም ፥ በአሁኑ ጊዜ በማይሠራባቸው ቃላት ወይም ቃላቱ ቢኖሩም ፥ ባሁኑ ጊዜ በማይሠራበት ትርጉም ። ለምሳሌ ፥ ቆቻ ፥ ቢያክ ፥ መራ ፥ ቆሌ በጥንቱ ትርጉማቸው አይሠራባቸውም ። ነገር ግን በነሱ ላይ የተመሠረቱት ፈሊጦች ፥ ቆቻ ዋለ ፥ ቢያክ ቢያክ አለ ፥ መራውን ወጣ ፥ ቆሌ ቢስ ይሠራባቸዋል ። በትርጉምም ረገድ በለስ ጣለ ፥ ጋኔን ለከፈው ፥ አጽመ ርስት ፥ ቡዳ ቀረጠፈው ፥ አቲቴያም (ግልፍተኛ ለማለት) ዐይነቶች በጥንት አገባባቸው ባይሠራባቸውም ፥ አዲስ ትርጉም ይዘው ለዘመናዊ ሐሳብ መግለጫዎች ሊውሉ ይችላሉ ።

የፈሊጣዊ አነጋገሮችን አነሣስ አንዳንድ ጊዜ ለመናገር ስንችል ፥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንችልም ። ፈሊጦች ከአንዳንድ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ስለሆኑ፥ከጊዜ ብዛት አንዳንዶቹ ባህላዊ ዘርፎች እየተረሱና በሌላ እየተለወጡ ከመሔዳቸው የተነሣ። ስለሆነም ባጠቃላይ አነጋገር ፥ በየሀገሩ የሚነገሩት የተለያዩ ቋንቋዎች አንዱ ከሌላው በመተርጎምና በመውረስ የአያሌ ፈሊጦች ምንጭ መሆናቸው አይካድም ። ደራሲያን ሌሎች ምንጮች ናቸው ። በዚያ ላይ ደግሞ ከውጭ አገር ቋንቋዎች እየተወረሱ የሚገቡ ፈሊጦች አሉ ። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያን በሚመለከት ፥ በተለይ የተለያዩ የውጭ አገር ቋንቋዎች በየትምህርት ቤቱ መሰጠት ከጀመሩ ወዲህ ፥ ከውጪ የሚወረሱት ፈሊጦች ብዛት ከቁጥጥር ውጪ እመሆን ደረጃ ደርሰዋል ፤ ለምሳሌ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን እንመልከት ፥—

| የተለመዱ | እምብዛም ያልተለመዱ |
| --- | --- |
| በቤቱ ሒሳብ | ወንበር መውሰድ |
| መድኃኒት መውሰድ | ቀዝቃዛ ጦርነት |
| ቁልፍ ቦታ | ገበታ መሥራት |
| መኪና መንዳት | ሊፍት መስጠት |
| ጸጉር መሰንጠቅ | ታክሲ መያዝ |
| ቀጠሮ መውሰድ | አብሮ መሔድ (ለልብስ) |
| ሚና መጫወት | ሰውን መዝጋት (ለማነጋገር አለፈለግ) |
| በፍቅር መውደቅ | ፈተና መቀመጥ(ማለፍ/መውደቅ) |
| ስብሰባ መጥራት | (ቤት ወዳጅን) ማውጣት |
| ጽዋ ማንሣት (ለመልካም ምኞት) | |



ፈሊጣዊ አነጋገር አንዳንድ ጊዜ የተለመዱትን የሰዋሰው ሕግጋት የሚጥስ ሆኖ ይቀርባል ። ስለሆነም እንዲህ ዐይነት የቃላት ግጥሚያ መታየት ያለበት ፈሊጡ የሚተላለፈውን መልእክት አዳክሞ ወይም አጠናክሮ ከማቅረቡ አንጻርም ጭምር መሆን ይኖርበታል ። የሰዋሰው ሕግጋት ከመሰበራቸው አንጻር ብቻ ሳይሆን ። ስለዚህ ሊነቀፍ አይገባውም ።

በፈሊጣዊ አነጋገር ሐሳብን በትክክልና በተዘናና መንገድ ማሸጋገር መቻልና በዚህ ዐይነትም ሌሎች የሚያስተላልፉለትን መልእክት መረዳት መቻል የቋንቋ ሰዉ አንደኛው ተቀዳሚ ተግባሩ ነው ። በእርግጥ በፈሊጥ አማካኝነት ፥ የሚነገረው ጽንሰ ሐሳብ በቀጥታም መንገድ ሊገለጽ ይቻላል ። ነገር ግን በፈሊጥ መልኩ እንደሚገለጸው ያለ ኃይለ ቃልና ማራኪነት አይኖረውም ። ለምሳሌ እላይ ከጠቀስናቸው ምሳሌዎች አንዱን 'ሆደ ሰፊ' የሚለውን ፥ ብንወስድ 'ታጋሽ፥ቻይ' በሚል ቃል ልንተካው እንችላለን ፤ ይሁንና ይህ እንደ'ሆደ ሰፊ'ያለ ኃይል ሊኖረው አይችልም ፤ አይኖረውም ። ከዚህ የተነሣ ነው ፥ ማነኛውም የቋንቋ ተማሪ ሰው አንድን ቋንቋ ሲያጠና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ላይ ትልቅ ትኩረት ማድረግ ያለበት ። ቋንቋውን ጥሩ አድርጎ ዐውቋል የሚያሰኘው አንደኛዉ መለኪያ የዚያን ቋንቋ ፈሊጣዊ አነጋገሮች በሚገባ ማጥናቱና ብተገቢው ቦታው ሊያውላቸው መቻሉ ስለሆነ ።

በአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችም ረገድ ፥ የአማርኛን ፈሊጣዊ አነጋገር ማጥናት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኝላቸዋል፤ ገለጻቸውን በኃይለ ቃል በማጠናከር ንግግራቸውንም ሆነ ጽሑፋቸውን ይበልጥ ሐሳብ ጨባጭነትና አስጨባጭነት እንዲኖረው ስለሚያደርገው። ለምሳሌ ፥ 'ከበደ ሁልጊዜ አፉን ይበላዋል' በማለት ፋንታ 'ሁልጊዜ መለፍለፍ ይወዳል ብንል'፥ሁለተኛዉ እንደ መጀመሪያው ያለ ጥንካሬ አይኖረውም ። እንዲሁም የሚከተሉትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከቀጥተኛ ትርጉማቸው ጋር ብንደረድራቸው እላይ የተገለጸው ምንኛ እውነት መሆኑን ልንረዳ እንችላለን ፤

| | |
| --- | --- |
| አፉን አዳጠው | ሳያስበው ክፉ ተናገረ |
| አፌን በዳባ | አልናገርም |
| እሳት አፍ | ለፍላፊ |
| እሳት ሆኗል | በጣም ተወድዋል |
| እስክስ አለብኝ | አፌዘብኝ ፥ አቃቂያለኝ |
| በጥፊ ወለወለው | በጥፊ ደጋግሞ መታው |
| ልቤ ወደቀባት | ወደድኳት ወዘተ . . . |

*ሆድ ለሆድ*—ሐሳብ ለሐሳብ
ሆድ ለሆድ ተገናኝተዋል ፤ በሐሳብ ተስማምተዋል

*ሆድ ሰጠ*—አሳቡን ነገረ
ለማንኛውም ሰው ሆድን መስጠት ጥሩ አይደለም ፤ ለማያውቁት ሁሉ ምስጢርን ማካፈል

*ሆድ ሲያውቀ ዶሮ ማታ*—ራስን መደለል
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ሆኖበታል ፤ ልቡ እያወቀው የማያገኘውን ይመኛል

*ሆድና ጀርባ*—ፈጽሞ አለመግባባት
ሆድና ጀርባ ከሆኑ ብዙ ጊዜያቸው ነው ፤ በመካከላቸው ስምምነት ከጠፋ

*ሆድ ዕቃ*— 1. ሰውነት
ሆድዕቃዬ አሯል ፤ ተበሳጭቻለሁ
— 2. በሆድ ውስጥ ያለ የሰውነት ክፍል ሁሉ

*የሆድ*—ምስጢር
የሆዱን ነግሬው ነበር ፤ የልቤን



# ለ

## ለመነ ፥

*ለመናት*—በግብረ ሥጋ እንገናኝ አላት
ለምኗት ነበር ፥ እርሷ ግን አልፈቀደችውም ፤ ለግብረ ሥጋ ጠይቋት ነበር

*መለመኛ ለጣ*—ፈጽሞ ደኸየ
*የልመና አህል*—ኮስማና

## ለመደ ፥

*በዘልማድ*—በተለምዶ
በዓሉ በዘልማድ የሚከበር ነው ፤ ምክንያቱ ግን አይታወቅም

*አይለመድ*—ሁለተኛ አይደገም
እንዲህ ያለው ነገር ሁለተኛ እንዳይለመድ ፤ ሁለተኛ እንዳይሠራ

*አይለምደኝም*—አልደግመውም
አባዬ አይለምደኝም ፤ ሁለተኛ አላደርገውም

## ለማ ፥

*አልሚና ለሚ*—ኮከባቸው የሚገጥም
እኔና እርሱ አልሚና ለሚ ነን ፤ በማንኛውም ነገር እንስማማለን

## ለሰለሰ ፥

*ተለሳለሰ*—ሥራ ፈቶ ተቀመጠ
ሥራ እንደሌለህ ተለሳልሰሃልሳ ! ተዝናንተህ ተቀምጠሃልሳ !

## ለሰነ ፥

*ልሳኑ ተዘጋ*—መናገር አቃተው
ልሳንህን ይዝጋው ! መናገር ይከልክልህ !

## ለቀለቀ ፥

*ለቀለቀኝ*—በከለኝ (ለነገር)
አንተ በሠራኸው እኔን ለምን ትለቀልቀኛለህ
የወንጀልህ ግብረ አበር ለምን ታደርገኛለህ ?

*ዋንጫ ልቀለቃ*—የአንገት እስክስታ

**ሮሮ ፥**

ሮሮ አይመረው—ጥቃት አይከብደው
ሮሮ አይከብደው ነው ፥ ከዚያ ሁሉ በኋላ ተመልሶ አዳብሉኝ ይላል ፥
በደል አይሰማ

**ሮጠ ፥**

ሲሮጡ ያሰሩት—በውል ያልታሰረ ፥ በችኮላ የታሰረ
ሲሮጡ ያሰሩት ሲሮጡ ይፈታል
አሯሯጠው—አጣደፈው
አጉል ምግብ በልቶ ተቅማጥ አሯሯጠው
የልም ሩጫ —1. ሳይሮጡ የሮጡ የሚመስል
—2. ከንቱ ሐሳብ
ይሯሯጣል—ያዝኩህ ያዝኩህ ይላል
እንዲያው ይሯሯጣል እንጂ ቋቱ ጠብ አላለለትም



# ሰ

***ሰለጠ ፥**

መስቀል ተሰላጢን—የዓለሙንም የሃይማኖቱንም የተማረ
ስልጣኑ ተያዘ—እንዳይቀድስ ተከለከለ
ቆሱ የመምሬ አስጋኽኝን ሥልጣን ይዘውበታል ፤ አግደውታል
ሰለጠነባቸው—በኋላ መጥቶ የበላያቸው ሆነ
ስልጡን አፍ—አለሁ አለሁ ባይ
ስልጡን እጅ—የሰው ዕቃ ከማንሣት የማይቆጠብ
ድህነት ሰለጠነ—እየከፋ ሔደ
ድህነት በሠለጠነበት በዚያ በቀውጢ ቀን ፤ በተስፋፋበት
ድንቁም ሰለጠነች—እንዲህ ያለም እውቀት የለ!
ክፉ ስልጣኔ—ተንኮል
እንዲህ ያለውን ክፉ ሥልጣኔ ብትተውስ ፤ ሸር

***ሰለፈ ፥**

ለነገር ተሰ...—ለሙግት ፥ ለክርክር አቆበቆበ
ለነገር ተሰልፈህ እስከ መቼ ትዘልቀዋለህ ለጭቅጭቅ ተዘጋጅተህ
ሰልፍህን አሳምር—ከሰው ተስማማ
ሰልፍ ወጣ—ለሰልፍ ሔደ
ለ.... አትሰለፍ—አትተባበር
ለክፉ ነገር አትሰለፍ ፥ አትተባበር
ሰልፍ አበላሸ—አይገቡ የሚገባ

**ሰመረ ፥**

ሰመር ገጠመ—አንቆ ያዘ
ሲታገሉ ሰመር ስለ ገጠመው ራሱን ማስለቀቅ አቃተው
ሰመር ገባ—ተያዘ ፤ ተሸነፈ
ሰመር ስለ ገባለት አንሥቶ አፈረጠው ፤ ሰቅስቆ ስለ ያዘው

ሾላ ፤

ሾላ በድፍን—ያልተገለጠ ነገር
ያንቀ ነገር ሾላ በድፍን ነው ፤ተከድኖ ይብሰል ፤ ድብቅ ነው

ሾመ ፤

ሹም ሽር—ሹመት
ሹመት ያዳብር—ሹመቱ እየጨመረ ይሒድ (ለተሾመ)
ሹመት ለይደንገጥ—እንደ ተሻርክ አትቅር (ሹመቱን ላጣ)
ዛሩ ተሾመ—ዛር ተነሣ
ደመናው ተሾመ—በአየር ላይ ተንሰራፋ
ጋኑ ተሾመ—ጋኑ ተሞላ

ሾረ ፤

ለአለቃ ይሾራል—ይስላል ፤እየተንቀጠቀጠ ይታዘዛል

ቯ አለ ፤

ቯ አለ—ፈሰሰ
ሽልንጉ አስፋልቱ ላይ ቯ አለ ፤ ተበተነ



# ቀ

ቀለለ ፤

መሬት ይቀለለው—መቃብሩ ይስማማው
በሰው ፊት ቀለለ—ተዋረደ
ቀ/ል ያለ—ቀትረ ቀላል
በሽታው ቀለለው—እየተሻለው ሔደ
ቀላል ሰው ነው—ለቁም ነገር የሚበቃ አይደለም
ቀትረ ቀላል—ከውካዋ ፣ ቀሌ ቢስ
ብስል ተቀሊል—ጥሩና መጥፎ ፣ ትንሽና ትልቅ
ተቃለለ—እያነሰ ሄደ
ለቃለለ—አራከሰ
ለነገሩ ቀለለ—ውሸት ሆነ
እግሩ ቀለለ—ፈጠነ
እግሩ ቀለለው መሰለኝ በቶሎ ደረሰ
ፈተና ቀለለ—ሳይከብድ ቀረ
ይቀለኛል—አልፈራውም ፣ አላፍረውም
ካለስ ጓደኞች ሁሉ አማረ ይቀለኛል ፤ ሳልፈራ አነጋግረዋለሁ

ቀለመ ፤

ቀለም አገባ—ነከረ
በሐዘኑ ምክንያት ቀሚሷና ኩታዋን ጥቁር ቀለም አገባች
የቀለም አባት—አስተማሪ
ቀለም ገባው—ትምህርቱን ተማረ ፤ እየገባው ሔደ
የቀለም ሰው—የትምህርት ሰው
የቀለም ቀንድ—ሊቅ ፣ ዐዋቂ ፣ ተመራማሪ

ቀለሰ ፤

መለስ ቀለስ—መመላለስ
መለስ ቀለስ ብሎ በሽተኛውን ጠየቀ ፤ ደጋግሞ
ለንገቱን ቀለሰ—አዘነ ፣ ተከዘ
ጐጆ ቀለሰ—ቤት ሠራ
ብዙ ጊዜ በደባልነት ቆይቶ በቅርቡ ጐጆ ቀለሰ

ቀለበ ፤

ቀለባት—ወዲያው ወሰዳት
ትምህርት ቀለበ—ቶሎ ገባው

አውራ ፡

አውራ ሊሊት—ውድቅት
አውራ መንገድ—ትልቅ ጐዳና
አውራ ሰው—1. የቤተ ሰብ ኃላፊ 2. እምነት የሚጣልበት ቁም ነገረኛ ሰው
አውራ በግ—ያልተቀጠቀጠ የበግ አውራ
አውራ ተሲያት—ቀትር ፡ ስድስት ሰዓት
አውራ ነገር—ቁም ነገር ፡ ርእሰ ነገር ፡ የነገር መሰረት
አውራ አዘል—ድርስ ጊደር
አውራ ከተማ—ዋና ከተማ
አውራ ጠላት—ክፉ ደመኛ
አውራ ጣቱን ጠባ—አላዋቂ ሆነ
አውራ ጣት—ወፍራም ጣት
አውራ ፍየል—ያልተወቀጠ ፍየል

አውሸለሸለ ፡

ነገረ ውሽልሽል—ቁም ነገር የሌለበት ፤ ውል የለሽ ነገር

አውተፈተፈ ፡

ውትፍትፍ ስራ—የይድረስ ይድረስ ስራ

አዘለ ፡

ለቆ አዘለ—የግብር ይውጣ ረጂ
ሲያዝሉት ይነጭ—ሲረዱት ፡ ሲደግፉት ይጎዳ
አዝሎ ኖረ—ሲረዳ ኖረ
አይኑ እንባ አዘለ—አይኑ እንባ ቋጠረ

አዘነ ፡

አዘን ተቀመጠ—ለቅሶኛ ተቀበለ
እዝን—ለሀዘንተኛ የሚወሰድ ምግብና መጠጥ

አዘዘ ፡

ሰውነቱ አልታዘዘው አለው—ሰውነቱ ደከመ
አዘዘበት—1. መከራ መጣበት
—2. ክፉ አጋጣሚ አጋጠመው
አዛዥ ናዛዥ—የበላይ አለቃ

አዛር ፡

አዛር ነፋበት—ተበላሸ



አዞረ ፡

ማዞሪያ—የስልክ ቤት
ራሱን አዞረው—1. አደናገረው
—2. ራሱ ዥው አለበት
—3. አሰከረው

አየ ፡

መታያ—ገጸ በረከት
መከራ አየ—መከራ ደረሰበት
ምን ታይተታል—ምን አስቧል
ምን አየብኝ—ምን ነካው ( ለታመመ ሰው )
ሰው አየ—ፈረደ
የሰው እጅ አየ—በሰጡኝ አለ ፤ ደኸየ
በጠላት አይን አየ—እንደ ጠላት አየ
ቢስ አይይህ—ክፉ ነገር አይግጠምህ
ባይኑ ቂጥ አየ—ገረመመ ፤ በንቀት ተመለከተ
አስተያየ—አወዳደረ
አታስተያየው—ስለእሱ አታስብ ( ለቅልሽልሽታ )
አዙሮ የማያይ—ይሉኝ የማይል
አየሁ አላለም—አልበቃውም ፤
ሶስት እንጀራ በልቶ አየሁ አላለም
አየሁለት—ታዘብሁት
አየህ! --ልብ አልከው !
አየህልኝ?—ነገሩን ተረድተኸዋል?
አየበት—1. መብላት ከለከለው ፤ ሳይበላ ጠገበ
— 2. ፈረደበት
— 3. የልቡ ክፋት ችግር አስከተለበት
አዩኝ አላዩኝ ብሎ—ተደብቆ ፡ ፈራ ተባ እያለ
አዩኝ አላዩኝ አለ—በስራ ሰነፈ ፤ ተደብቆ ክፋት ሰራ
እሳት አየው—እሳት ነካው ( ቢበስልም ባይበስልም )
እግዜር አየ—ፈረደ
ክፉ አይይህ—ክፉ አይድረስብህ
የጎድን አየ—አይኑን አጣሞ አየ ፤ በንቀት ተመለከተ

አያት ፡

ከአያት ከቅድማያት—ከብዙ ትውልድ ጀምሮ

አይን ፡

አይነ ልም—ተንኮለኛ
አይነ ሊባ—አመንዝራ ፡ ሸርሙጣ
አይነ ስጋ—በሕይወት
በአይነ ስጋ ለመገናኘት ያብቃን ፤ በሕይወት ቆይተን
አይነ ስቡን አለው—አይኑን አንጎደው ፤ መታው
አይነ ስውር—አይኑ የማያይ ፡ እውር

**ኮከብ ፡**

ኮከበ ነጠላ—እድለ ቢስ
ኮከባቸው ገጠመ—ተፋቀሩ ፤ ተዋደዱ
ኮከበ ሠራተኛ—በጣም ትጉ ሠራተኛ
ኮከበ ቀጣሪ—ጠንቋይ
ኮከበ ተዋናይ—ዋና ተዋናይ

**ኳለ ፡**

ባለኩል—ቆንጆ
ኩል የመሰለ ውሃ—የጠራ ውሃ
ተኳኩላ ቀረበች—ራሷን አሳምራ
የተኳለ የተዳረ—ወግ ማረግ የደረሰው

**ኰሰኰሰ ፡**

የሚኩሰኩስ ባህርይ ሰለው—ለሰው የማይመች

**ኰነነ ፡**

ሰታስኩነኝ—አጉል አታናግረኝ ፤ የማላውቀውን

**ኳስ ፡**

ኳስ ሜዳ—የኳስ መጫወቻ ሜዳ
ኳስ ራስ—ድቡልቡል ራስ
ኳስ ሰበደች—በኳስ ድብድብ ተጀመረ
የመረብ ኳስ—መረብ እያዘለሉ የሚጫወቱት ኳስ
የቀርጫት ኳስ—በጉንጉን ክር ውስጥ እያገቡ የሚጫወቱት ኳስ
የእግር ኳስ—በእግር እየመቱ የሚጫወቱት ኳስ
የኳስ ዳኛ—ኳስ አጫዋች

**ኳኳቴ ፡**

ኳኳቴያም—ቅራቅምቧም

# ወ

**ወህኒ ፥**

ወህኒ ሆኗል—የሚያሰቃይ ነው
ወህኒ ለገባ—እሰረ

**ወለለ ፥**

ልቡ ወልል አለ—ተሸበረ ፤ ታወከ
ለውላላ ሜዳ—1. ሰፊ ሜዳ
—2. የትም ፤ አልባሌ ቦታ
ወለላዩ—የማታስቀይመኝ ፥ የማታስቀይሚኝ
ወለል ያድርገኝ—እኔን ያስደንግጠኝ
ወለል አለ—ነጋ ፤ ጠራ
የዛሬው ቀን ወለል ብሎዋል
ወላላ—ሆደ ሰፊ
ወለል አደረገ—ከፈተ

**ወለምታ ፥**

ወለም ዘለም አለ—አልጨበጥ አለ
ምነው ወለም ዘለም አበዛህ ? በቃልህ አልረጋ አልክ
ያፍ ወለምታ—ሳያስቡት በንግግር መሳሳት
ያፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም

**ወልቀ ፥**

ልቡ ወልቋል—መስሎታል
ሠራሁ ብሎ ልቡ ወልቋል
ልቤን ለታውልቀኝ—አትነዝንዘኝ
ልብሱን ለወለቀ—ራቁቱን ቀረ
ልብ አውልቀ—ነዝናዛ
ሱሪ በራስ አውልቀ—የማይቻል ነገር አድርግ ማለት
ያንተ ትእዛዝ ሱሪ በራስ አውልቁ ነው
ሱሪዩ በራሴ ወልቋል—የወንድነት እሞቱ ፈሷል !
ሲያዋርደኝ ዝም ታልኩትማ ሱሪዩ በራሴ ወልቋል ማለት ነዋ !
ቁራ ያወለቀው—ጉድጓዳ ዐይን
ቂጡ ወልቋል—ከስሯል ፤ ነፍሶበታል

ድብ ፡

ድብ ለንበሳ—ትልቅ ነጋሪት

ድጓ ፡

ድጓ ወሣው—ዜማ አዋቂ

ድፍን ፡

ድፍን ቅል—ደንቆሮ ፤ ደደብ
ድፍን ለቆረጠ—ወንድም ፣ ተካፋይ



# ጀ

ጀመረ ፡

መናገር ጀመረ—አፍ ፈታ
ቤት ጀመረ—ቆረቆረ ፤ መሠረተ
ትምህርት ጀመረ—ፊደል መማር ያዘ
ጠብ ጀመረ—ጠብ አጫረ

ጀንበር ፡

የሁዳዴ ጀንበር—ሠራተኛ ሰው

ጂኒ ፡

ጂኒያም—ተናዳጅ

ጃን ፡

ጃን ደረባ ለደረገ—ሰለለ
ጃን ገበር—ኮከብ ገበሬ

ጅም ፡

ጅም ታለህ—በጅምህ ተጫወት
ጅም ታለኝ—በጅሜ እጫወታለሁ

ጅራት ፡

ጅራት ለበቀለ—ተናደደ ፤ እንደ እብድ አደረገው
ጅራቱን ይቆላል—ይለማመጣል

ጅብ ፡

ጅብ አፍ—ሰፊ አፍ
የቀን ጅብ—ርህራሄ የሌለው ፣ ስግብግብ
ያፈና ጅብ—በጣም የተራበ ፤ ስግብጋብ
ጆቦ—ጉበዙ ( ለሥራ )

*ጐለለ ፡

ለንጓለለ—በንቀት አይን ተመለከተ

ጐለመሰ ፡

ለእምሮው ጐለመሰ—አእምሮው አደገ ፤ ዕውቀት ገባው

ጐለበተ ፡

በጉልበቱ ኖረ—በሀይሉ ኖረ
እየጐለበተ ሄደ—እየተጠናከረ ሄደ
ጉልበተኛ—በሀይሉ ተጠቃሚ
ጉልበታም—ሀይለኛ ፡ አመጸኛ
ጉልበት አወጣ—ሀይል አገኘ
ጉልበቱን ለፈሰሰ—ስራ ሰራ

ጐለጐለ ፡

መሬቱን ጐለጐለ—አራሙቻውን አነሳ
ምላሱን ጐለጐለ—ብዙ ተናገረ
ለይኑን ጐለጐለ—አፍጦ አየ
የሰው ምስጢር ጐለጐለ—የሰው ምስጢር ዘከዘከ

ጐመን ፡

ከሁለት ያጣ ጐመን—ከሁለት ወዳጅ የተጣላ
ጐመን በጤና—ከነገር መሸሽ
ከሥጋ ብስና ጐመን በጤና

ጐረፈ ፡

ብዙ ሰው ወደ ገበያ ጐረፈ—በብዛት ሄደ
ጐረፍ ጐረፍ ለደረገው—ላይ ላዩን ሰራ

ጐበኘ ፡

ለልፎ ለልፎ በሽታ ይጐበኘዋል—ያስቃየዋል

ጐነጐነ ፡

ነገር መጐንጐን ይወዳል—ነገር መጠምዘዝ ይወዳል



ጐን ፡

ለጐኑ ያውቃል—ለራሱ ያውቃል
ጐንና ጐን—ግራና ቀኝ

ጓሮ ፡

ለምባጓሮ—ጥል
ጓሮ ዞሯል—ለመጸዳዳት ወደ ውጭ ሄዷል ፤ አፍአ ወጥቷል
ጓሮ ጓሮውን ይላል—ዳር ዳሩን ያንጃብባል

ጓዝ

ጓዝ ተጋዥ—አንድ ወታደር ከነቤተሰቡ
ጓዝ ተጋሽ ቀለብ—የባልና የሚስት ቀለብ

ጓዳ

ጓዳዩን ያውቀዋል—ምስጢሩን ያውቀዋል
ጓዳ ጐድጓዳ—የቤት ስርቻ ፡ ውስጣ ውስጥ

ጥጃ ፥

ክርሞ ጥጃ—የማይሻሻል ፥ የማያድግ
ጥጃ ሆድ—ትንሽ ሆድ
ጥጃ አሰረ—ላሙ ወለደችለት

ጥግ ፥

ባለጥግ—ባልወገን
ጥገኛ—ራሱን ችሎ የማይኖር
ጥግ ጥጉን አትበል—ደፍረህ ተናገር ፥ ፈራ ተባ አትበል

ጥፊ ፥

ቃሪያ ጥፊ—በእጅ ጀርባ የሚመታ ጥፊ
ጥፊ መታው—ፊቱ አበጠ
ጥፊ ወጥ—አንድ ጊዜ በተቆፈለ እንጀራ ተነክሮ የሚወጣ ወጥ፥ የማታበላ ወጥ

ጥፍር ፥

ጥፍሪም—ዓለኔ

ጦለ

ልበ ጡል—ዝንጉ

ጦመ ፥

ለፋ አይጦምም—ዝም አይልም
ለፍህ ይጡም—የምትናገረውን ምረጥ ፥ አትቅለብለብ
እጅህ ይጡም—አትስረቅ
እግርህ ይጡም—እርፈህ ተቀመጥ
የጦም—በጦም የማይበላ
የጦም ወጥ—በጦም ቀን የሚበላ ( ስጋና ቅቤ ወዘተ.የሌለበት )

ጦር ፥

የጦር ለፎ—የጦርነት እቅድ የሚማር ጀማሪ
የጦር ባል—የጦር ስልት አዋቂ
ጦሩ ተፈታ—ወታደሩ ሸሸ
ጦር ማቆሚያ—አባት ለልጁ በተለይ የሰጠው መሬት
ጦር ሰራ—ክተት አለ ፥ አዘጋጀ
ጦር ሻረ—የጠላቱን ጦር ድል ነሳ
ጦር ተፈታ—ተሸነፈ ፥ ድል ሆነ
ጦር ነቀለ—1.ጦርን አነሳ ፥ ያዘ
—2.ጦር መላሽ ፥ አፋለኛ ፥ ጉበዝ



ጦር አፍ—ነገረኛ
ጦር ጠማሽ—ዘመቻ ፈላጊ ፥ ወያኔ ፥ ፋኖ

ጡጣ ፥

ጠጣ እየሆንክ ሂደሃል—ሞኤ እየሆንህ

ጭ. አለ ፥

እልልክ ባተ

ጥራ ቀረሽ—ቀዥቃዣ ፡ እብድ
ጥሬው አይያዝም—ሞላጫ ፡ ሸለከላካ ነው
ጥሬውን ለበሰ—ፈረጠጠ
ጥሬውን ሸጉበ—አንገቱን ደፋ
ጥሬውን ነሰነሰ—መስሎ ለመታየት ፈለገ
ጥሬውን ነከሰ—ኮራ
ጥሬውን ለማታ—ተለማመጠ
ጥሬውን አያስይዝም—ራሱን ያድናል
ጥሬው ጮሌ—ብልጣ ብልጥ

ጥራቅ ፡

ጥሬቅ ነው—ብልህ ነው

ጥር ፡

ጥር ለለች—ጫጩቶቿን አስጠነቀቀች

ጥቃ ፡

በየጥቃው—በየመንደሩ
ነገሩ ጥቃ ነው—የሚናገረው ለሰሚ አይጥምም
ነገሬን በጥቃ ውስጥ ጉተተው—ዋጋ አሳጣብኝ
እንደ ጥቃ ረገጠው—አበክሮ መታው
ጥቃ ሱሪ—በክረምት የሚለበስ ሱሪ
ጥቃ ለፍ—1.ከንፈረ ጥቁር ሰው
—2.ነገር ለዳፊ

ጥን ፡

የጥን በቅሎ—ባለቤቷ ብቻ የሚቀመጣት በቅሎ
የጥን ገረድ—እንደ ሚስትም እንደ አገልጋይም ሆና የምትኖር ሴት
ጥን ጠባቂ—ብርቱ ፈረሰኛ

ጥው ፡

ጥው ጥው አለ—ከሳ ፡ ደረቀ (ለሰው)
ጥው ያለ በረሃ—ሰፊ ምድረ በዳ

ጥዳ ፡

ጥዩ አለ—ሰውን ገደለ

ጥጥ ፡

ጥጥ ምጥጥ የለም—ዝም ብሎ መስራት ነው



ጮሌ ፡

ጮሌ ፈረስ—ፈጣን ፡ ሸምጣጭ ፈረስ

ጮቤ ፡

ጮቤ መታ—በተረከዙ ቂጡን መታ

ጮኸ ፡

ለዳኛ ጮኸ—ለዳኛ አቤት አለ
[illegible]
ጩኸቴን ቀሙኝ—እኔ በተበደልሁ ያልተበደሉት ይናገሩ ጀመር
ጩኸቱ ትርፉ—አቤት አቤቱ እንጂ ምንም አላገኘሁ ፤
ከንቱ ልፋት
ጮኸ—ዜማ ተማረ
ጮኸበት—ተቆጣው

# ጸ/ፀ

**ፀሀይ ፡**

ጸሀይ ወጣ—እውነቱ ተገለጠ

**ጸሎት ፡**

የሽኮኮ ጸሎት—መጨረሻው የማያምር ነገር

**ፀያፍ ፡**

ጸያፉን ከተተ—ነውሩን ሰወረ

**ጽድቅ ፡**

ጽድቅና ኩነኔ—ጥቅምና ጉዳት

**ጸጋ ፡**

ጸጋ አደረበት—ጸጋ ለበሰ



# ፈ

**ፈለሰ ፡**

በኩርኩም አፈለሰው—በኩርኩም መታው
ፍልስልሱ ወጣ—ተመነገለ ፡ ተደመሰሰ

**ፈለቀ ፡**

መብረቁ ፍልቅ ፍልቅ አለ—ብልጭ ድርግም አለ
ደሟ ፍልቅ ያለ—የሚያምርበት
ጥሩ ሐሳብ አፈለቀ—አመጣ
ፍልቅልቅ—ሳቂታ ፡ ሁልጊዜ ፈገግታ የማይለየው

**ፈለገ ፡**

ምን ትፈልጋለህ ?—ምን ከጅሎሃል ፤ ምን ይሻሃል ( ለጥል )
ሰገር ተፈረሰ ለስፈለገ—ባስቸኳይ አስፈለገ
ተፈላለገ —ለጥል ተከጃጀለ
እንደ ፈለገው ነው—እንዳሻው ነው
ፈልገኛል—ከጅሎኛል
ፍላጎቱን ተወጣ—አምሮቱን ተወጣ

**ፈለጠ ፡**

ራሴን ፈለጠኝ—ራስ ምታት ይዞኛል
የምጋ ቁራጭ ያጥንት ፍላጭ—የቅርብ ዘመድ
ፈላጭ ቆራጭ—ለሥልጣኑ ወሰን የሌለው ፡ አምባገነን

**ፈለፈለ ፡**

ብዙ ልጅ ፈልፍሏል—ወልዷል
ነገር ፈልፍሎ አወጣ—ምስጢር ከተደበቀበት አወጣ
ፈልፋይ—ነገረኛ ፡ ተንኮለኛ
ፍልፍል ጥርስ—የሚያምር ፡ የተስተካከለ ጥርስ

**ፈላ ፡**

ቀማል ፡ ትኋን ፡ ቁንጫ ወዘተ. ፈላበት—በብዛት ወጣበት
ግላውን አረም ፈላበት
ወናው ቤት ቁንጫ ፈልቶበታል ፤ አያስገባም

ፍንጭ ፡

የነገር ፍንጭ—የነገር ትንሽ ክፍል ፡ ምልክት

ፍየል ፡

ፍየል ለፍ—ቀባጣሪ ፡ ለፍላፊ
ፍየሏን እንደ በግ ብላቧን እንደ ሞኝ

ፍዳ ፡

ፍዳውን አየ—መከራውን ተቀበለ
ፍዳዬን በላሁ—መከራ አየሁ